# ሰባት ደብዳቤዎች
# ለአጥቢያ
# ቤተ ክርስቲያናት

## ክፍል አንድ

ከካሣሁን ደጉ ተተረጐመ

# ሰባት ደብዳቤዎች
# ለአጥቢያ
# ቤተ ክርስቲያናት

በግሎብ የሥነ ጽሑፍ ድርጅት
፲፱፻፸ ዓ. ም. ተዘጋጀ ።

መ. ማ. ቁ. 4798

አሳታሚው በጽሑፍ ካልፈቀደ በቀር ይህንን መጽሐፍ
ወይም የመጽሐፉን ክፍል በምንም ዓይነት መልክ
ገልብጦ ማቅረብ የተከለከለ ነው ።

No Portion of this book may be reproduced
without written permission of the Publisher.

## ጠቅላላ መልእክቶች

1. ያዕቆብ
2. 1ኛ እና 2ኛ ጴጥሮስ
3. 1ኛ ፣ 2ኛ ፣ 3ኛ ዮሐንስና ይሁዳ

# ማ ው ጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| የመጽሐፉ አጠቃቀም | |
| 1ኛ ሳምንት ፡— ያዕቆብ | 9 |
| 1ኛ ቀን ፡— ደብዳቤዎቹ የተጻፉት ለምን ነበር? | 15 |
| 2ኛ ቀን ፡— ያዕቆብ አገልጋይ ነበር ፤ ለአይሁድም ጻፈ | 23 |
| 3ኛ ቀን ፡— ፈተና ክርስቲያኖችን ብርቱ ያደርጋቸዋል | 29 |
| 4ኛ ቀን ፡— ምኞት ኃጢአትን ኃጢአትም ሞትን ያመጣል | 37 |
| 5ኛ ቀን ፡— ንጹሕ ሃይማኖት ምንድር ነው? | 45 |
| 2ኛ ሳምንት ፡— ያዕቆብ | |
| 1ኛ ቀን ፡— የንጉሡ ሕግ ምንድር ነው? | 53 |
| 2ኛ ቀን ፡— እምነት ያለ ሥራ የሞተ ነው | 61 |
| 3ኛ ቀን ፡— አንደበት እንደ እሳት ነው | 68 |
| 4ኛ ቀን ፡— በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠብን የሚያስነሣ ምንድር ነው? | 76 |
| 5ኛ ቀን ፡— በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተነሣውን ጠብ እንዴት እንደምናቆም | 85 |

## ማውጫ

3ኛ ሳምንት ፡— ያዕቆብ

1ኛ ቀን ፡— ክርስቲያኖች ገንዘብን መውደድ አይገባቸውም ...... ...... ...... 95

2ኛ ቀን ፡— ክርስቲያኖች የጌታን መመለስ በትዕግሥት ይጠባበቃሉ ...... 105

3ኛ ቀን ፡— ክርስቲያኖች መማል አይገባቸውም ...... ...... ...... ...... ...... 113

4ኛ ቀን ፡— ቤተ ክርስቲያን ለሕሙማን ትጸልያለች ...... ...... ...... ...... 121

5ኛ ቀን ፡— ወደ ኋላ የተመለሱትን ወንድሞች ወደ እውነት መልሰህ አምጣቸው ...... ...... ...... ...... 130

## የመጽሐፉ አጠቃቀም

ይህ መጽሐፍ አስተማሪህ ነው ። በየዕለቱ አንድ ትምህርት ያስተምርሃል ። መጽሐፉ የሚልህን በጥንቃቄ አድምጥ ። በደንብ ለመማር ከፈለግህ ልክ አስተማሪህን እንደምትታዘዝ መጽሐፉን መታዘዝ አለብህ ። አስተማሪህ መጽሐፍ ቅዱስህን አውጥተህ አንድ ጥቅስ እንድታነብ ቢነግርህ ዝም ብለህ አስተማሪህን ትመለከታለህ ? አትመለከትም ። በኋላ አውጥቼ አነባለሁ ትለዋለህ ? አትልም ። መጽሐፍ ቅዱስህን ወዲያው አውጥተህ ታነባለህ ። በዚህ መጽሐፍም መጠቀም ያለብህ እንዲሁ ነው ። እንደ አስተማሪህ ታዘዘው ።

አንድ አስተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዴት እንደሚያስተምር አስብ ። በመጀመሪያ ተማሪዎቹን አንድ ነገር ይነግራቸዋል ። ይህንንም ነገር በደንብ ያብራራላቸዋል ። ከዚያም ጥያቄ ይጠይቃል ። ተማሪዎቹ በትክክል ቢመልሱ መልሳቸው ልክ መሆኑን ይነግራቸዋል ። በትክክል ባይመልሱ ግን ትምህርቱን እንደገና ያብራራላቸዋል ።

ይህ መጽሐፍም የሚያስተምረው በዚሁ መንገድ ነው ። በመጀመሪያ ትንሽ ትምህርት ይሰጥሃል ። ከዚያም ጥያቄ ይጠይቅሃል ወይም አንድ የምትሠራው ነገር ይሰጥሃል ። በጥንቃቄ ካነበብህ ጥያቄውን ለመመለስ ትችላለህ ። ጥያቄዎቹ ትምህርቱ በደንብ ገብቶህ እንደሆነ ያሳያሉ ። ከዚህም በላይ የተማርከውን እንድታስታውስ ይረዱሃል ።

ትምህርቱ የተዘጋጀው እያንዳንዱን ክፍል በጥንቃቄ ስታነብ ትክክለኛውን መልስ እንድታገኝ ተደርጎ ነው ። ስለ መልሱ እርግጠኛ ካልሆንህ ያንን ክፍል ደግመህ ማንበብ ይገባሃል ። አሁንም እርግጠኛ ካልሆንህ ልትመልስ የምትችለውን ጽፈህ እለፍ ። በትክክል መመለስህን ወይም አለመመለስህን በሚቀጥለው ትምህርት ውስጥ ልታገኝ ትችላለህ ። ሆኖም ተከታዩን ትምህርት ከማንበብህ በፊት መልሱን ለመስጠት መሞከር አለብህ ። ይህ በጣም አስፈላጊ ነው ። ስታነብ ቀሪውን ክፍል ወፈር ባለ ወረቀት ብትሸፍነው በደንብ እንድትመልስ ይረዳሃል ። ወረቀቱን ቀጥለህ ወደምታገኘው ______ እንዲህ ዓይነቱ መስመር ድረስ ዝቅ ልታደርገው ትችላለህ ። ትምህርቱን አንብብና ጥያቄውን መልስ ። ከዚያም ወረቀቱን ወደሚቀጥለው መስመር ዝቅ አድርገው ። በዚህ መንገድ ጥያቄውን ለመመለስ ከመሞከርህ በፊት መልሱን አታንብም ።

ይህ መጽሐፍ የጠቅላላ መልእክቶች የመጀመሪያው ክፍል ነው ። በዚህ ክፍል ያዕቆብ ለአጥቢያ ቤት ክርስቲያናት የጻፈውን ደብዳቤ ታጠናለህ ።

መጽሐፉን ለመጨረስ ሦስት ሳምንቶች ይፈጅብሃል ። በየዕለቱ አንድ ትምህርት በመሥራት ለሳምንቱ የተሰጡትን የአምስት ቀናት ትምህርት ትጨርሳለህ ። በአንድ ቀን ሁለት ወይም ሦስት ትምህርቶችን ለመሥራት አትሞክር ። በየትምህርቱ መጨረሻ የሚቀርቡት ጥያቄዎች በጣም ጠቃሚ ናቸው ። አስተማሪህ እንድታውቅ የሚፈልገው ምን እንደሆነ ያሳዩሃል ። እነዚህን የመጽሐፉ ግብ እንላቸዋለን ። በሳምንቱ መጨረሻ ላይ በየዕለቱ ትምህርት ግርጌ የተሰጡትን ጥያቄዎች በሙሉ መልስህ ከሆነ በደንብ ተምረሃል ማለት ነው ።



ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ሳምንታዊ በሆነ የውይይት ስብሰባ ላይ እንዲያገለግል ታስቦ ነው ። በችግርህ የሚረዳህ አንድ መሪ ሊኖርህ ይገባል ። መሪህ ከመጽሐፉ የተማርከውን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር እንድትወያይ ይረዳሃል ። ወደ ክፍል ከመምጣትህ በፊት ትምህርቶችህን ያላጠናህ ከሆነ ውይይቱ ሊገባህ አይችልም ።

ትምህርቶቹን እንድታጠና የሚረዳህ መሪ ካላገኘህ ጓደኞችህን ጥራ ። ትምህርቱን ወስደው እንዲያጠኑ ጠይቃቸው ። ከዚያም በአንድነት ተሰብስቡና ተወያዩ ። ውይይቱንም እንዳችሁ ልትመሩ ትችላላችሁ ።

የትምህርቱን አቀራረብ እንደምትወደው እንገምታለን ። በምታጠናበት ሰዓት ትክክለኛውን መልስ ለማግኘት በጣም መጣር አለብህ ። መልሱን ካገኘህ ትደሰታለህ ። በመጽሐፉ መጨረሻ ወደሚገኙት ጥያቄዎች ስትመጣ ምን ያህል መማርህን በመገንዘብ ትደነቃለህ ።

# ክፍል አንድ

## ያዕቆብ

## 1ኛ ሳምንት

### 1ኛ ቀን ፡— ደብዳቤዎቹ የተጻፉት ለምን ነበር ?

1. በሚቀጥሉት ሦስት ሳምንታት ከእናንተ ጋር በየዕለቱ እንነጋገራለን ። እግዚአብሔር ሁላችንንም እንዲያስተምረን ጸልዩናል ። የእግዚአብሔርን ሥራ በተሻለ መንገድ ለመሥራት መማር እንፈልጋለን ።

   ብዙ ሰዎች ደብዳቤ ማግኘት ይወዳሉ ። ወዳጆቻችን ከእኛ ርቀው ሲኖሩ ደብዳቤ ሲጽፉልን እንወዳለን ። ወሬያቸውን ለመስማት እንፈልጋለን ።

   ደብዳቤ ማግኘት ደስ ያሰኝሃልን ? ______________

   ______________________________________

   ______________________________________

2. ሁላችንም ደብዳቤ ስናገኝ እንደሰታለን ። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ሐዋርያት ስሌሎች ክርስቲያኖች ደብዳቤ እንዲጽፉ እግዚአብሔር ረዳቸው ። እነዚህ ደብዳቤዎች አንዳንድ ጊዜ «መልእክቶች» ተብለው ይጠራሉ ። መልእክት የደብዳቤ ሌላ ስም ነው ።

   በዚህ መጽሐፍና ከዚህ ቀጥለው በሚወጡት ሁለት መጻሕፍት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለሚገኙ ሰባት ደብዳቤዎች እናጠናለን ። እነዚህ ሰባት ደብዳቤዎች ጠቅላላ መልእክቶች ይባላሉ ። ደብዳቤዎቹ የተጻፉትም ለክርስቲያኖች ሁሉ ነው ።

ክርስቲያኖችን ለማበረታታት የተጻፉትን ሰባቱን ደብዳቤዎች የምንጠራቸው ምን ብለን ነው ? ______

______

11. ጠቅላላ መልእክቶች እንላቸዋለን ። እነርሱም በብዙ በተለያዩ ሥፍራዎች ለሚኖሩ ክርስቲያኖች በሐዋርያት የተጻፉ ናቸው ።

ጠቅላላ መልእክቶች የተጻፉበት ሁለተኛው ምክንያት ሐሰተኛ ትምህርትን ለማረም ነው ። በዚያን ዘመን ራሳቸውን እንደ አስተማሪ የሚቆጥሩ ብዙ ሰዎች ነበሩ ። እነዚህ ሰዎች ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ይዘዋወሩ ነበር ። አንዳንዶቹ ጥሩ አስተማሪዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ሐሰተኞች ነበሩ ። እውነትን አያስተምሩም ነበር ።

ጠቅላላ መልእክቶች የተጻፉበት የመጀመሪያው ምክንያት ምንድር ነው ?

ሀ) ______
ለ) ሐሰተኛ ትምህርትን ለማረም

12. ክርስቲያኖችን ለማበረታታት ነው ። ይሁን እንጂ ምክንያቱ ይህ ብቻ አልነበረም ። ሁለተኛው ምክንያት ሐሰተኛ ትምህርትን ለማረም ነበር ። ሐሰተኛ አስተማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን የማያስተምሩ ሰዎች ናቸው ። እነዚህ ሰዎች እውነትን አያስተምሩም ። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን አንዳንድ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ክርስቶስ አምላክ



አይደለም እያሉ አስተማሩ ። አንዳንዶቹ ደግሞ ክርስቶስ ዳግመኛ ተመልሶ አይመጣም ይሉ ነበር ።

ሐዋርያት እነዚህን ሰባት ደብዳቤዎች የጻፉት እውነትን ለማስተማርና ሐሰተኛ ትምህርትን ለማረም ነበር ።

ሐሰተኛ አስተማሪ የሆኑ ሰዎችን ታውቃላችሁን ?

______

ምዕመናን ሐሰተኛ ትምህርትን ለማረም የሚሆን ስብከት ያስፈልጋቸዋል ? ______

______

13. ዛሬም በአንዳንድ ሥፍራዎች ሐሰተኛ አስተማሪዎች ይገኛሉ ። እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን አያስተምሩም ። መጽሐፍ ቅዱስን በትክክለኛው መንገድ አይተረጉሙም ። ጠቅላላ መልእክቶች በተጻፉበት ዘመንም እንዲሁ ነበር ።

ጠቅላላ መልእክቶች የተጻፉበት ሁለተኛው ምክንያት ምንድር ነው ? ______

______

14. ሐሰተኛ ትምህርትን ለማረም ነው ። ሐሰተኛ ትምህርት መጥፎ ነገር ነው ። ክርስቲያኖችን በኢየሱስ እንዳያምኑ ሊያደርጋቸው ይችላል ። ብዙ ችግሮችንም ይፈጥራል ።

ዛሬ በአንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙት ሰዎች በእውነተኛና በሐሰተኛ ትምህርት መካከል ያለውን ልዩነት አያውቁም ። በአንዳንድ ሥፍራዎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ደህና አድርጎ የሚተረጉም ጥሩ አስተማሪ የለም ። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ ካልተረዱ ሐሰተኛ ትምህርትን ማዳመጥ ይጀምራሉ ።

ሐዋርያት ጠቅላላ መልእክቶችን ለሁለት ምክንያቶች ጻፉ ። የመጀመሪያው ምክንያት ምንድር ነው ?

ሀ) ______________________

ለ) ሐሰተኛ ትምህርትን ለማረም፡



1ኛ ሳምንት

2ኛ ቀን ፡— ያዕቆብ አገልጋዩ ለአይሁድ ጻፈ

1. ትላንትና ጠቅላላ መልእክቶች ለሁለት ታላላቅ ምክንያቶች እንደተጻፉ ተምረናል ።
ምክንያቶቹን ጻፍ ።

ሀ) ______________________

ለ) ______________________

---

2. ጠቅላላ መልእክቶች የተጻፉት ክርስቲያኖችን ለማበረታታት እና ሐሰተኛ ትምህርትን ለማረም ነበር ። ዛሬ የያዕቆብን ደብዳቤ ማጥናት እንጀምራለን ። አስቀድመን ደብዳቤውን ስለ ጻፈው ሰው እንመልከት ። የሚጽፍልህን ሰው ማወቅ የተገባ ነው ። ዛሬ የምንማረውም ይህንኑ ነው ።

ሀ) ያዕቆብ ራሱን አገልጋይ ብሎ ይጠራል
ለ) ያዕቆብ ለተበተኑት አይሁዶች ደብዳቤውን ጻፈ

ትምህርቱን ከመቀጠልህ በፊት መጽሐፍ ቅዱስህን አውጣና ያዕቆብ 1፥1 አንብብ ።

---

3. ከእነዚህ ጥቅሶች ይህንን ደብዳቤ የጻፈው ያዕቆብ የሚባል ሰው መሆኑን እናያለን ። ትላንትና የኢየሱስ ወንድም የነበረውን ያዕቆብን... 

16. ፈተናዎች ሲገጥሙን ደስ ልንሰኝ ይገባል ። እግዚአብሔር በፈተና ውስጥ ደስተኞች እንድንሆን ይፈልጋል ። ስለዚህ እግዚአብሔርን ማማረር አይገባንም ። መንፈስ መራሮች መሆን የለብንም ። ችግር ሲገጥመን ስለ ሌሎች ክፉ ማውራት አይገባንም ። በዚያ ፈንታ ችግር ሲገጥመን ደስ ልንሰኝ ይገባናል ፤ ምክንያቱም ፈተናን በሚገባ መቋቋም ብርቱዎች ያደርገናልና ።

በመከራ ውስጥ የሚያልፉ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ ። አሁን እንኳን በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ችግር ያለባቸው ክርስቲያኖች ይኖሩ ይሆናል ። እነዚህ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ይህ ችግር የደረሰባቸው ለምን እንደሆነ አያውቁም ።

ወደ ክፍል ከመምጣትህ በፊት አንድ ችግር ያጋጠመውን ሰው ጐብኝ ። በተማርከው ትምህርትም በመጠቀም ፈተናው እንዴት ሊረዳው እንደሚችል አስረዳው ።

---

17. ያደረከውን ነገር በክፍል ውስጥ ተነጋገሩበት ።

የእምነታችን በችግር መፈተን የሚረዳን እንዴት ነው ? ______________________

ፈተና ሲገጥመን ምን ሊሰማን ይገባል ? __________

______________________________



1ኛ ሳምንት

4ኛ ቀን ፦ ምኞት ኃጢአትን ኃጢአትም ሞትን ያመጣል (ያዕቆብ 1፡9—15)

1. ትላንትና እምነታችንን ለመፈተን ችግር እንደሚገጥመን አይተናል ።

የእምነታችን በችግር መፈተን የሚረዳን እንዴት ነው ? ______________________

ፈተና ሲገጥመን ምን ሊሰማን ይገባል ? __________

______________________________

---

2. የእምነታችን በችግር መፈተን ብርቱዎች ያደርገናል ። ስለዚህ ፈተና ሲገጥመን ደስ ልንሰኝ ይገባናል ።

ፈተና አንድ መጥፎን ነገር ለማድረግ መመኘት ነው ። ዛሬ ስለ ፈተና ሁለት ነገሮችን እንማራለን ።

ሀ) አንዱ የፈተና መነሾ የራሳችን መጥፎ ፍላጐት ነው

ለ) በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአት እንዲነግሥ ከፈቀድን እንሞታለን

አሁን መጽሐፍ ቅዱስህን አውጣና ያዕቆብ 1፡9—15 አንብብ ።

ክርስቲያኖች ኃጢአትን ለመሥራት ይፈተናሉ ብለህ ታስባለህ ? ___

___

3. ክርስቲያኖች ኃጢአትን ለመሥራት ሲፈተኑ ይች ላሉ ። ይህ የሚሆነው ለምንድር ነው ?

ምክንያቱን ያዕቆብ በምዕራፍ አንድ ቁጥር አሥራ አራት ላይ ይነግረናል ።

እያንዳንዱ (ሰው) በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል ። ይህም ፥ ፈተና ሰው በገዛ ራሱ ክፉ ምኞትና ሐሳብ ጐትቶ የሚያመጣው ነገር ነው ማለት ነው ። ፈተና ትክክል ያልሆነን ነገር ለማድረግ መፈለግ ነው ።

ያዕቆብ 1፥14 እንደገና አንብብ ። ይህ ጥቅስ ፈተናን የሚያመጣው ሰይጣን ነው ይላል ? ___

___

4. ጥቅሱ ፈተናን የሚያመጣብን ሰይጣን ነው አይልም ።

ጥቅሱ የሚለው የገዛ ራሳችን ምኞት እንድንፈተን ያደርገናል ነው ።

ግርማ በከፋ ክፍለ ሀገር በአንዲት ትንሽ መንደር ውስጥ ይኖራል ። አንድ ቀን ወደ ጅማ ከተማ መጣ ። በከተማው ውስጥ ብዙ ሊያደርጋቸው የሚፈልጋቸውን ነገሮች አየ ። መጠጥ የሚጋብዙትንም ወዳጆች አፈራ ። ሰዎቹ ደስተኞች ይመስላሉ ። መጥፎ ነገር እንዲያደርግም የምትገፋፋው አንዲት ሴት አገኘ ። ግርማ በጣም ተፈተነ ።



ግርማን እንዲፈተን ያደረገው ምንድር ነው ? የገዛ ራሱ ፍላጐት ወይስ ሰይጣን ? ___

___

5. ግርማን እንዲፈተን ያደረገው የልቡ ምኞት ነው ። ጓደኞቹ የነበራቸው ነገር እንዲኖረው ፈለገ ። እነርሱ ያደረጉትንም ለማድረግ ፈለገ ። ግርማ እነዚህ ምኞቶች ነበሩት ፤ እነዚህም ምኞቶች ፈተኑት ።

እርግጥ ነው ዲያብሎስ አንዳንድ ጊዜ ይፈትነናል ። ኢየሱስን የፈተነው ዲያብሎስ ነበር ። (ማቴዎስ 4፥1 ተመልከት)

ዲያብሎስ ኢየሱስን ፈተነው ። ነገር ግን ፈተና የሚመጣው ከዲያብሎስ ብቻ ነው ? ___

___

6. አብዛኛውን ጊዜ የምንፈተነው በገዛ ራሳችን መጥፎ ምኞት ነው ። የፈተና ምንጭ ዲያብሎስ ብቻ አይደለም ። መቼም አንዱ ምክንያት እርሱ ነው ። ሌላው የፈተና ምንጭ የራሳችን መጥፎ ሐሳብ ነው ። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር አታድርጉ ያለንን ነገር ለማድረግ እንፈልጋለን ።

የገዛ ራሳችን ምኞት ምን ያደርገናል ? ___

___

ይዘን ከሆነ በሕይወታችን ይገለጣል ። በኃጢአት ውስጥ እንመላለሳለን ።

አንዱ የፈተና ምንጭ ዲያብሎስ ነው ። ሌላውስ የፈተና መነሾ ምንድር ነው ? ________________

________________________________________

________________________________________

11. ክርስቲያኖች በኃጢአት ከጸኑ ይሞታሉ ። ያዕቆብ 1፥15 የሚለው ይህንኑ ነው ። ኃጢአት በሕይወታችን ውስጥ ከተስፋፋ ሞትን ያመጣል ። ጥቅሱ የሚናገረው አንድ ጊዜ ብቻ ኃጢአትን ስለሚሠራ ሰው አይደለም ፤ ነገር ግን ሁልጊዜ ኃጢአትን እየሠራ ኃጢአቱን ስለማይናዘዘው ሰው ነው ።

በልባችን ውስጥ ክፉ ምኞት እንዲኖር ከፈቀድን በመጨረሻ ምን ይሆናል ? ________________

________________________________________

________________________________________

12. በልባችን ውስጥ ክፉ ምኞት እንዲኖር ከፈቀድን በመጨረሻ ኃጢአትን ለመሥራት እንገደዳለን ። ኃጢአትን እንሠራለን ። በልባችን ውስጥ ክፉ ምኞት እንዳይኖር መጠንቀቅ አለብን ። ክፉ ምኞቶችን ከልባችን ውስጥ ማስወገድ ይገባናል ። ሕይወታችንን መልካም በሆኑ ምኞቶች መሙላት አለብን ።



ያዕቆብ በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአት እንዲነግሥ ብንፈቅድ ምን ይሆናል አለ ? ________________

________________________________________

________________________________________

13. በመንፈስ እንሞታለን ይላል ። ነገር ግን እግዚአብሔር እንድንሞት አይፈልግም ። ሕይወት እንዲኖረን ይፈልጋል ። ፈተናን እንድናሸንፍና ድል እንድና ደርግ ይፈልጋል ። ለዚህ እንዲረዳን እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ተስፋዎች ሰጥቶናል ። (1ኛ ቆሮንቶስ 10፥13 እና ያዕቆብ 4፥7 ተመልከት)

ከዚህ ትምህርት እንደምናገኘው በመንፈስ ልንሞት የምንችለው እንዴት ነው ? ________________

________________________________________

________________________________________

14. ኃጢአታችንን ካልተናዘዝንና በኃጢአት ውስጥ መመላለሳችንን ካልተውን በመንፈስ እንሞታለን ።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የምናገኘው የሳምሶን ታሪክ ይህንን ያሳየናል ። ሳምሶን በልቡ ውስጥ መጥፎ ምኞት እንዲነግሥ ፈቀደ ። በዚህም የተነሣ የኃጢአት ተገዥ ሆነ ። በመጨረሻም መንፈሳዊ ሕይወቱን አጣ ።

ይህንን ትምህርት ከጨረስህ በኋላ የሳምሶንን ታሪክ ከመሳፍንት 13፥24—16፥31 አውጣና አንብብ ።

15. ያዕቆብ እንደሚነግረን ከሰይጣን ቀጥሎ ሁለተኛው
የፈተና ምንጭ ምንድር ነው ? ______

______

በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአት እንዲነግሥ ብንፈ
ቅድ ምን የሚሆን ይመስልሃል ? ______

______



1ኛ ሳምንት

5ኛ ቀን ፡— ንጹሕ ሃይማኖት ምንድር ነው ? (ያዕቆብ 1፡16—27)

1. ትላንትና ስለ ፈተና ተማርን ። እግዚአብሔር በፈ
ተና ላይ ኃይል ሊሰጠን ይፈልጋል ።

ያዕቆብ እንደሚነግረን ከሰይጣን ቀጥሎ ሁለተኛው
የፈተና ምንጭ ምንድር ነው ? ______

______

በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአት እንዲነግሥ ብንፈ
ቅድ ምን የሚሆን ይመስልሃል ? ______

______

______

2. ዛሬ ከያዕቆብ ደብዳቤ ውስጥ በቃላችን ሁለት ጥቅ
ሶች ለመያዝ እንሞክራለን ። ጥቅሶችን በቃላችን
ብናጠና መጽሐፍ ቅዱስ በሌለን ጊዜ ጥቅሶቹን በቃ
ላችን ለማለት እንችላለን ። ሁለቱ ጥቅሶች በጣም
ጠቃሚ ስለሆኑ በደንብ አድርገህ አጥናቸው ።

ያዕቆብ 1፡19—20 ፡—

ስለዚህ ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ፥ ሰው ሁሉ
ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቁጣም የዘ
ገየ ይሁን ፤ የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ
አይሠራምና ።

6. ያዕቆብ ፣ ንጹሕ ሃይማኖት ያለው ሰው ወላጆች የሌላቸውን ልጆችና መበለቶችን ይጐበኛል ይላል ። ያዕቆብ እነዚህ ሰዎች በችግርና በስቃይ ውስጥ ያሉናቸው ይላል ።

በአካባቢህ ብዙ እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች አሉ ። ብዙ የተለያዩ ችግሮች ያሉአቸው ሰዎች አሉ ።

ለእነዚህ ሰዎች ምን ማድረግ አለብኝ ብለህ ታስባለህ ? ______________________

______________________

7. ያዕቆብ ልንጐበኛቸው ይገባል ይላል ። ወደ እሉበት በመሄድ ችግራቸውን ልናቃልልላቸውና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ልንረዳቸው ይገባናል ።

በቅርቡ የሐና ባለቤት ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ። ሐና አራቱን ልጆችዋን ለብቻዋ ማሳደግ ጀመረች ። በአጠገቧ ዘመዶችዋ የሉም ። ሐና በታላቅ ሐዘን ውስጥ ነበረች ። ይህ ለእርስዋ ከባድ ፈተና ነበር ። ሐና የምታመልክበት ቤተ ክርስቲያን መሪ ከባለቤቱ ጋር ሆኖ ሐናን ለማጽናናት መጣ ። ከሐናም ጋር አብረው ጸለዩ ፤ ረዱአትም ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትንም ሌሎች ሴቶች ወደ ሐና ዘንድ ሄደው ርዳታ እንዲያደርጉላት ጠየቋአቸው ። ይህ ድርጊት ሐናን አበረታታት ፤ በእግዚአብሔር ላይ ያላትንም እምነት አጠነከረላት ።

መበለቶችንና ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ልጆች የሚጐበኙ ሰዎች ያላቸው ሃይማኖት ምን ዓይነት ነው ? ______

______________________

______________________



8. ንጹሕ ሃይማኖት ነው ። አንዳንድ ሰዎች በእግዚአብሔር እንደሚያምኑ ይናገራሉ ። ንጹሕ ሃይማኖት አለን ይላሉ ። አንዳንዶቹም ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ይጸልያሉ ። ነገር ግን ሰውን ፈጽሞ አይረዱም ። ከኃጢአትም አይርቁም ። እነዚህ ሰዎች ንጹሕ ሃይማኖት የላቸውም ።

ንጹሕ ሃይማኖትን የሚያመለክተው የመጀመሪያው ነገር ምንድር ነው ? ______________________

______________________

9. ንጹሕ ሃይማኖትን የሚያመለክተው የመጀመሪያው ነገር መበለቶችንና ወላጆች የሌላቸውን ልጆች መጐብኘት ነው ። ችግረኞችን እቤታቸው ድረስ እየሄድን መጠየቅ ይገባናል ። ከዚህ ቀጥለን ንጹሕ ሃይማኖትን የሚያመለክተውን ሁለተኛውን ነገር እንመለከታለን ። (ያዕቆብ 1፥27 አንብብ)

ንጹሕ ሃይማኖት ያለው ሰው ሊያደርገው የሚገባው ሁለተኛው ነገር ምንድር ነው ? (መልሱን ካነበብከው ጥቅስ ውስጥ ፈልግ) ______________________

______________________

10. ንጹሕ ሃይማኖት ያለው ሰው ራሱን በዓለም ከሚገኝ እድፍ ይጠብቃል ። እስቲ ይህ ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት ። ከዕለታት አንድ ቀን ባለቤቴ በቤታችን ውስጥ ለእንግዶች ቡና ታሳልፍ ነበር ። ስታሳልፍም በእንድዋ እንግዳችን ቀሚስ ላይ ቡና አፈሰሰች ። ቡናውም ልብሱን አጠቆረውና አበላ

ራስህን ከዓለም እድፍ መጠበቅህ ምንን ያሳያል ?—

______________________________

15. ንጹሕ ሃይማኖት እንዳለህ ያሳያል ። ክርስቲያኖች ስለዚህ ነገር በጣም መጠንቀቅ ይገባቸዋል ። ዮሐንስ ስለዚሁ ነገር በደብዳቤው ውስጥ ጽፎአል ።

1ኛ ዮሐንስ 2፥15 ፥—

ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ ፤ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም ። ንጹሕ ሃይማኖትን የሚያሳዩት ሁለቱ ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

ሀ) ____________________

ለ) ____________________

16. ንጹሕ ሃይማኖትን የሚያሳዩ ሁለት ነገሮች አሉ ። የመጀመሪያው መበለቶችንና ወላጆች የሌላቸውን ልጆች መጠየቅ ሲሆን ፥ ሁለተኛው ደግሞ ከዓለም እድፍ ራስን መጠበቅ ነው ። እነዚህ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ሊገኙ የሚገቡ ነገሮች ናቸው ። በተለይም በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ውስጥ ሊገኙ ይገባቸዋል ።

ይህ የመጀመሪያው ሳምንት ትምህርት መጨረሻ ነው ። ያዕቆብ ምዕራፍ አንድን ጨረስን ። ጥሩ ሠርተሃል ። አሁን ራስህን ዝቅ አድርግና እግዚአብሔርን በዚህ ሳምንት ትምህርት ስለረዳህ አመስግነው ።



2ኛ ሳምንት

1ኛ ቀን ፥— የንጉሡ ሕግ ምንድር ነው ? (ያዕቆብ 2፥1—13)

1. ባለፈው ሳምንት ንጹሕ ሃይማኖትን የሚያሳዩ ሁለት ነገሮች እንዳሉ ተምረናል ። እነዚህ ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

ሀ) ____________________

ለ) ____________________

2. የመጀመሪያው መበለቶችንና ወላጆች የሌላቸውን ልጆች መጠየቅ ሲሆን ፥ ሁለተኛው ደግሞ ከዓለም እድፍ ራስን መጠበቅ ነው ። ዛሬ ያዕቆብ ምዕራፍ ሁለትን ማጥናት እንጀምራለን ። በዛሬው ትምህርታችን ሁለት ነገሮች እንመለከታለን ።

ሀ) በሰዎች መካከል ብናዳላ ኃጢአትን እንፈጽማለን ።

ለ) የንጉሡ ሕግ ፥ «ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ» ይላል ።

ባለፈው ሳምንት ያዕቆብ 1፥19—20 አጠናን ። መጽሐፍ ቅዱስህን ሳትመለከት ከዚህ በታች ጻፈው ።

______________________________

______________________________

3. በትክክል ጽፈዘ እንደሆን ለማየት መጽሐፍ ቅዱስህን ተመልከት ። አሁን የምታጠናቸው ሁለት መጻሕፍት እንዳሉ እንድታስታውስ እንፈልጋለን ። የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን ሁለተኛው ይህ አሁን የምታነበው መጽሐፍ ነው ። እነዚህን ትምህርቶች ለታጠና መጽሐፍ ቅዱስህን ማንበብ አትርሳ ። አሁን መጽሐፍ ቅዱስህን አውጣና ያዕቆብ 2፡1—13 አንብብ ።

ቁጥር 9 በድጋሚ አንብብ ። በዚህ ጥቅስ መሠረት በሰዎች መካከል ስናዳላ ምን ማድረጋችን ነው ? ______

______________________________

______________________________

4. መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ስናደርግ ኃጢአትን እንሠራለን ይላል ። በሰዎች መካከል ብናዳላ ኃጢአትን እንፈጽማለን ። ሰዎችን ሁሉ እኩል ካልተመለከትን እግዚአብሔርን እንበድላለን ።

ያዕቆብ ባለጠጎችን ባለጠጎች ስለሆኑ የተለየ ክብር ብንሰጣቸው ኃጢአትን እንሠራለን ይላል ። ድሆችንም ስለ ድህነታቸው ዝቅ አድርጎ ማየት ኃጢአት ነው ። ባለሥልጣኖችን ማክበር አስፈላጊ ነው ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ እኩል ማየቱን መርሳት የለብንም ።

በሚቀጥለው እሑድ አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ወደ ቤተ ክርስቲያንህ ቢመጣ ምን ታደርጋለህ ? ______

______________________________

______________________________



5. መልስህን በክፍል ውስጥ እንነጋገርበታለን ። መሪዎቻችንን ማክበር የተገባ ነው ፤ ነገር ግን መሪዎቻችን በእግዚአብሔር ፊት ከሌሎች ሰዎች ጋር እኩል መሆናቸውን አንርሳ ። ድሆችን መርሳት የለብንም ። ከፍተኛ ሥፍራ የሌላቸውንም ሰዎች ዝቅ አድርጎ መመልከት አይገባንም ።

ያዕቆብ 2፡9 ፡—

ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራላችሁ

በዚህ ጥቅስ መሠረት ኃጢአት ልንሠራ የምንችልበት አንዱ መንገድ ምንድን ነው ? ______

______________________________

______________________________

6. በሰዎች መካከል ማዳላት ነው ። ይህንን ማድረግ አይገባንም ።

ያዕቆብ 2፡1 ፡

ወንድሞች ሆይ ፣ በክብር ጌታ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን እምነት ለሰው ፊት በማድላት አትያዙ ።

በምዕራብ ኬንያ አንድ በጣም ሀብታም የሆነ ሰው አለ ። ይህ ሰው ብዙ ሚስቶች አሉት ። ለእግዚአብሔር የማይኖር ሰው ቢሆንም እንኳ አንዳንድ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል ። ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚመጣበት ጊዜም መሪው የተለየ መስተንግዶ ያደርግለታል ። መሪው ባለጠጋው ሰውዬ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ገንዘብ ይሰጥ ይሆናል ብሎ ያስባል ። ይህ ባለጠጋ በቤተ ክርስቲያን

ብዙ ሰዎች እንደነበሩ ይናገራል ። እነዚህ ሰዎች እውነተኛ እምነት ካላቸው መልካም ሥራ ይሠሩ ነበር ። ይህ ፡ እምነታቸው ሕያውና እውነተኛ መሆኑን ያሳያል ።

ለምሳሌ ፣ ወደ ሠፈራችን አንድ እንግዳ ሰው ይመጣል እንበል ። ሰውየውም በኢየሱስ እንደሚያምንና ክርስቲያን እንደሆነ ይነግረናል ። እንግዲህ የዚህ ሰው እምነት ሕያውና እውነተኛ መሆኑን እንዴት ልናውቅ እንችላለን ? ____________________

---

8. አንዱ መንገድ ሰውየው የሚያደርጋቸውን ነገሮች መመልከት ነው ። በሕይወቱ ውስጥ በጐ ምግባር እንዳለ ለማየት ትችላለህ ። ሕመምተኞችንና በችግር ውስጥ ያሉትን ሰዎች የሚረዳ ከሆነ እምነቱ ሕያው ነው ማለት ነው ። የእግዚአብሔርንም ቃል የሚከተል ከሆነ እውነተኛ እምነት አለው ማለት ነው ።

ያዕቆብ እምነታችን ሕያው መሆኑን ለማሳየት በጐ ምግባር ሊኖረን ይገባል ብሎ ያስተምራል ። በጐ ምግባር ወይም መልካም ሥራ ከሌለን እምነታችን የሞተ ነው ። በእርግጥም እምነት የለንም ማለት ነው ።

ለመዳን እንድንችል በልባችን ውስጥ ምን መኖር አለበት ? ____________________

---

9. ለመዳን በልባችን ውስጥ እምነት መኖር አለበት ። በኢየሱስ ማመን አለብን ። ነገር ግን እምነት አለኝ



ብሎ ማውራቱ በጣም ቀላል ነው ። በኢየሱስ እናምናለን ብሎ መናገርም አስቸጋሪ አይደለም ። ያዕቆብ አጋንንት እንኳን ያምናሉ ብሎ ተናግሮአል ። ነገር ግን አጋንንት አይድኑም ።

ያዕቆብ 2፡19 ፡—

እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ ፤ መልካም ታደርጋለህ ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል ።

ለመዳን በኢየሱስ ማመን አለብን ። ነገር ግን ያዕቆብ እምነታችን ሕያውና እውነተኛ መሆኑን ለማሳየት ምን ሊኖረን ይገባል ይላል ? ____________________

---

10. በጐ ምግባር ሊኖረን ይገባል ። በጐ ምግባር የምንለው አንድ ሰው የሚፈጽመውን መልካም ሥራ ነው ፤ ችግረኞችን በምንረዳበት ጊዜ መልካም ሥራ መሥራታችን ነው ። መበለቶችንና ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ስንጠይቅ መልካም ሥራ መሥራታችን ነው ። ለእግዚአብሔር ቃል ስንታዘዝም መልካም ሥራ መሥራታችን ነው ።

መልካም ሥራ በልባችን ውስጥ ምን ሕያው ነገር እንዳለ ያሳያል ? ____________________

---

ውስጥ ይገኝ እንደሆነ ራስህን ጠይቅ ። የሰላምና የአንድ ነት ሰው ለመሆን እንዲረዳህ እግዚአብሔርን ጠይቅ ።

---

16. ትላንትና እርስ በርስ መተማማት ጠብን እንደሚ ፈጥር ተማርን ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠብ የሚያስነሡ ሦስቱ ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

ሀ) ______________

ለ) ______________

ሐ) ______________



2ኛ ሳምንት

5ኛ ቀን ፦ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተነሣውን ጠብ እንዴት እንደምናቆም (ያዕቆብ 4፡7—10)

1. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠብን የሚያስነሡ አራት ነገሮች እንዳሉ ተምረናል ። በመጀመሪያ እርስ በርስ መተማማት ጠብን እንደሚፈጥር ተመስከ ትን ። ከዚያም ሌሎች ሦስት የጠብ መነሻ ምክን ያቶች ተማርን ።

እነዚህ ሦስት ምክንያቶች ምንና ምን ናቸው ?

ሀ) ______________

ለ) ______________

ሐ) ______________

---

2. ሦስቱ ነገሮች መመኘት ፣ ዓለምን መውደድና ትዕ ቢት ናቸው ። ነገር ግን ማንኛችንም በቤተ ክርስቲ ያን ውስጥ ጠብ እንዲኖር አንፈልግም ። የምንፈል ገው ፍቅርና አንድነትን ነው ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ኅብረት የሚያመጡ ነገሮችን ለማድረግ እን ፈልጋለን ። ዛሬ የምንማረው ስለ እነዚህ ነገሮች ነው ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠብ እንዳይፈጠር ልንፈጽማቸው የምንችል ሦስት ነገሮች አሉ ።

ሀ) ራስህን በእግዚአብሔር ፊት አዋርድ

ለ) ዲያብሎስን ተቃወም

ሐ) በቅድስና ኑር

10. ከሚቃወሙት ዘንድ ይሸሻል ። ትቶን ይሄዳል ። እስቲ ስለ ቄስ ጽጌ እንደገና እናስብ ። ሰዎች ስለ እርሱ የሚያወሩትን በሰማ ጊዜ ምን እንደተሰማው አስብ ። ቄስ ጽጌ ቤተ ክርስቲያኒቱን ትቶ እንዲሄድ ሰይጣን ሐሳብ ሰጠው ። ወደ ሰዎቹም ቤት ሄዶ እጥ ብቆ እንዲቃወማቸው አሳሰበው ። ነገር ግን ቄስ ጽጌ እነዚህን ነገሮች ለማድረግ አልተሸነፈም ። ለሰይጣን የእምቢታ መልስ ሰጠው ። ከሁሉ አስቀ ድሞ ራሱን በእግዚአብሔር ፊት አዋረደ ።

ከዚያ በኋላስ ምን አደረገ ? ______________

______________________________

11. ዲያብሎስን ተቃወመ ። ቄስ ጽጌ ዲያብሎስ ሑከትን ለማስነሣት የሚያስችለውን አንድም ነገር አልሠራም። ዲያብሎስ ግን በጣም ፈተነው ። ባሙት ሰዎች ላይ ክፉ ቃል ለመናገር ተፈተነ ። ነገር ግን ለዲያብሎስ ለመታዘዝ አልፈለገም ፤ ዲያብሎስን ተቃወመ ። በዚህም ምክንያት በፈተናው አሸነፈ ።

ኢየሱስ በተፈተነ ጊዜ ዲያብሎስን ተቃወመ ። ከዚ ያም ዲያብሎስ ተወው ። እኛም ዲያብሎስን እን ድንቃወም ኢየሱስ ይረዳናል ። ዲያብሎስ የኢየሱ ስን ኃይል ይፈራል ።

ዲያብሎስን ከተቃወምን ፣ ምን እንዳይነሣ እናደር ጋለን ? ______________



12. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠብ እንዳይነሣ እናደርጋ ለን ። ከያዕቆብ ደብዳቤ የጠቀስነው ክፍል ጠብን ለማቆም የሚረዳንን ሌላውን መንገድ ይነግረናል ። በቅድስና መኖር አለብን ። በቅድስና የሚኖር ሰው ንጹሕ ሕይወት አለው ። ንጹሕ ልብ አለው ። ከእግ ዚአብሔር አጠገብ ፣ በእግዚአብሔር ውስጥ ይኖ ራል ።

ያዕቆብ 4፥8 ፦

. . . . . . ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል ። እናንተ ኃጢአተኞች ፣ እጆቻችሁን አንጹ ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ ፣ ልባችሁን አጥሩ ።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነሣውን ጠብ ለማቆም ልናደርጋቸው የሚገቡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

ሀ) ______________

ለ) ______________

ሐ) በቅድስና ኑር

13. ዲያብሎስን መቃወምና ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት ማዋረድ አለብን ። ሆኖም ይህ ብቻ በቂ አይደለም ። በቅድስና መኖርም አለብን ። በቅድስና የሚኖር ሰው «ንጹሕ እጆች» አሉት ። ይህም በእጆቹ የሚጠቀ መው የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ነው ማለት ነው ። በእጆቹ መጥፎ ነገሮችን ለመሥራት አይጠ ቀምም ። ሕይወቱም የመጥፎ ነገሮች መፈጸሚያ

ያንህ ውስጥ ጠብ ቢኖር ምን ማድረግ ያለብህ ይመስል
ሃል ? የምታስበውን ከዚህ በታች ጻፍ ። ______

______

______

______

______

17. ያዕቆብ በሚነግረን መሠረት ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነሣውን ጠብ ለማቆም ልናደርጋቸው የሚገቡን ሦስት ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

ሀ) ______

ለ) ______

ሐ) ______



3ኛ ሳምንት

1ኛ ቀን ፦— ክርስቲያኖች ገንዘብን መውደድ አይገባቸውም (ያዕቆብ 4፥13—5፥6)

1. ዛሬ ክርስቲያኖች ስለ ገንዘብ ያላቸው አስተሳሰብ ምን መሆን እንዳለበት እንማራለን ። ክርስቲያኖች በገንዘብ ፍቅር ሲያዙ ሁለት ታላላቅ ነገሮች ይሆናሉ ።

   ሀ) ለእኔ ብቻ የሚሉ ራስ ወዳድ ይሆናሉ ።

   ለ) ፍርደ ገምድል ይሆናሉ ።

በትላንትናው ትምህርት መሠረት ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነሣውን ጠብ ለማቆም ልናደርጋቸው የሚገቡን ሦስት ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

ሀ) ______

ለ ______

ሐ) ______

______

2. ሦስቱ ነገሮች ፦— ራስህን በእግዚአብሔር ፊት አዋርድ ፣ ዲያብሎስን ተቃወም ፣ በቅድስና ኑር የሚሉ ናቸው ። እነዚህን ነገሮች ካደረግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነሣውን ጠብ ለማቆም እንችላለን ።

ጢሞቴዎስ ፡ የእግዚአብሔር ሰው ፡ ከምን መሸሽ
ነበረበት ? ________________

________________

________________

16. ከገንዘብ ፍቅር መሸሽ ነበረበት ።
ገንዘብን መውደድ ሰዎች ምን እንዲሆኑ ያርደጋል ?

ሀ) ________________

ለ) ________________



3ኛ ሳምንት

2ኛ ቀን ፡— ክርስቲያኖች የጌታን መመለስ በትዕግሥት ይጠባበቃሉ (ያዕቆብ 5፡7—11)

1. ትላንትና ስለ ገንዘብ ፍቅር ተማርን ።
ገንዘብን መውደድ ሰዎች ምን እንዲሆኑ ያደርጋል?

ሀ) ________________

ለ) ________________

2. የገንዘብ ፍቅር ሰዎች ለእኔ ብቻ የሚሉ ራስ ወዳድና ፍርደ ገምድል እንዲሆኑ ያደርጋል ።

ዛሬ ደግሞ ክርስቲያኖች መከራና ችግር ሲያጋጥማቸው እንዴት መኖር እንደሚገባቸው እንመለከታለን ። ያዕቆብ የጌታን መመለስ በትዕግሥት መጠባበቅ ይገባናል ይላል ። እንዲሁም በመከራና በሥቃይ ውስጥ ታማኝ ስለነበረው ስለ ኢዮብ ይነግረናል ።

ጠቅላላ መልእክቶች የተጻፉበት ሁለት ምክንያቶች አሉ ። የመጀመሪያው ምክንያት ምንድር ነው ?

ሀ) ________________
ለ) ሐሰተኛ ትምህርትን ለማረም

3. የመጀመሪያው ምክንያት ክርስቲያኖችን ለማበረታታት ነው ። ያዕቆብ ደብዳቤውን የጻፈላቸው ሰዎች

ፈተና ሲገጥመን ምን ሊሰማን ይገባል ? ______

______

16 በፈተና ደስ ልንሰኝ ይገባል ። ትዕግሥተኞችም መሆን ይኖርብናል ። እንደ ኢዮብ መሆን አለብን ። የኢየሱስን መመስስ በትዕግሥት መጠባበቅ አለብን ። መምጣቱን ስናስብ ተስፋችን ያድጋል ።

ምናልባትም ምዕመናንህ መበረታታት ያስፈልጋቸው ይሆናል ፤ ወይም ስለ ታላቁ ተስፋ ልታሳስባቸው ያስፈልግ ይሆናል ።

በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ምዕመናንህን ለማበረታታት ለምታዘጋጀው መልእክት የሚረዱህን ሐሳቦች ጻፍ ። በዚህ ትምህርት ውስጥ ባገኘሃቸው ነገሮች ተጠቀም ። ከቻልክ መልእክቱን እሑድ ዕለት አቅርበው ። ማስታወሻ ደብተርህን ወደ ክፍል ይዘኸው ና ።

17 ያዕቆብ ክርስቲያኖች የጌታን መመለስ እንዴት መጠበቅ ይገባቸዋል ይላል ?

ያዕቆብ በመከራ ውስጥ ስንሆን ከብሉይ ኪዳን የማንን ምሳሌነት እንከተል ይላል ? ______

______



3ኛ ሳምንት

3ኛ ቀን ፦ — ክርስቲያኖች መማል አይገባቸውም (ያዕቆብ 5፥12)

1. በትላንትናው ትምህርት መሠረት ክርስቲያኖች የጌታን መመስስ እንዴት መጠበቅ ይገባቸዋል ?

______

ያዕቆብ በመከራ ውስጥ ስንሆን ከብሉይ ኪዳን የማንን ምሳሌነት እንከተል ይላል ? ______

______

2. ክርስቲያኖች የጌታን መመስስ በትዕግሥት መጠበቅ ይገባቸዋል ። በፈተና እንደ ኢዮብ ብርቱዎች መሆን አለብን ።

ዛሬ ስለ መሐላ እንማራለን ። ክርስቲያኖች ለምን መማል እንደማይገባቸው የሚያሳዩ ሁለት ነገሮች አሉ ።

ሀ) ክርስቲያኖች ዘወትር እውነት መናገር ስለሚገባቸው

ለ) ሁልጊዜ ቃላቸውን መጠበቅ ስላለባቸው

በወገኖችህ መካከል አንዳንድ ጊዜ ሰዎች አንድ ዓይነት ስምምነት ለማድረግ መሐላ ይፈጽማሉን ? ______

______

ውም ። ቃላቸውን እንደሚጠብቁም ለማሳየት ሌላ ተጨ
ማሪ ነገር ማድረግ አይገባቸውም ። ክርስቲያኖች ቃላቸ
ውን ማክበርና እውነትን መናገር አለባቸው ። እነዚህን
ሁለት ነገሮች ከፈጸሙ መማል የለባቸውም ።

ስለ ራስህ አስብ ። ኢየሱስ መማል አይገባህም ይላል ።
ራስህን እነዚህን ጥያቄዎች ጠይቅ ። አዘወትሮ ቃሉን የሚ
ጠብቅ ሰው ነህ ? ሁልጊዜ እውነት ትናገራለህ ? ጐረቤቶ
ችህና የሥራ ጓደኞችህ ሊታመኑብህ ይችላሉ ? ማንበብ
ህን አቁምና ስለነዚህ ነገሮች ጸልይ ።

---

15. ክርስቲያኖች መማል የማይገባቸው ለምንድር ነው ?

ሀ) ____________________

ለ) ____________________



3ኛ ሳምንት

4ኛ ቀን ፡— ቤት ክርስቲያን ለሕሙማን ትጸልያለች

1. ትላንትና ክርስቲያኖች መማል እንደማይገባቸው ተምረናል ። መሐላ ማድረግ የለባቸውም ።

   ክርስቲያኖች መሐላ መፈጸም የማይገባቸው ለምንድር ነው ?

   ሀ) ____________________

   ለ) ____________________

---

2. ክርስቲያኖች ዘወትር እውነትን መናገርና ቃላቸውንም መጠበቅ ይገባቸዋል ። እነዚህን ነገሮች ከፈጸሙ መማል የለባቸውም ።

ዛሬ ደግሞ አንድ ሰው በሚታመምበት ጊዜ ቤት ክርስቲያን ምን ማድረግ እንዳለባት እንማራለን ። ምዕመናን በሚታመሙበት ጊዜ ሦስት ነገሮች ማድረግ ይገባቸዋል ።

ሀ) የቤት ክርስቲያኒቱን መሪ ጥሩ

ለ) እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ

ሐ) አንዳችሁ ስለ አንዳችሁ ጸልዩ

5ኛ ቀን ፦ ወደ ኋላ የተመለሱትን ወንድሞች ወደ እውነት መልሰህ አምጣቸው ። (ያዕቆብ 5፥19—20)

1. ዛሬ የያዕቆብ መጽሐፍ ጥናታችንን እንጨርሳለን ። ሆኖም ጥናታችንን ከመጨረሳችን በፊት የምንመለከተው አንድ አጠር ያለ ነገር አለ ። ከዚያ በኋላ ከያዕቆብ መጽሐፍ የተማርነውን ትምህርት በመከለስ ጥናታችንን እንፈጽማለን ።

በሕመም ጊዜ ልናደርጋቸው የሚገቡን ሦስት ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

ሀ) ____________________

ለ) ____________________

ሐ) ____________________

---

2. በምንታመምበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችንን መሪ መጥራት ይገባናል ። እርስ በርሳችን በኃጢአታችን መናዘዝና አንዳችን ስለ አንዳችን መጸለይ ይገባናል ።

ዛሬ ደግሞ አንድ የእምነት ወንድማችን ወደ ኋላ በሚመለስበት ጊዜ የምናደርገውን እንማራለን ። አንድ ክርስቲያን እምነቱን በሚተውበት ጊዜ ክርስቲያን ወንድሞቹ ወደ እውነት ሊመልሱት መጣር ይገባቸዋል ።

ሰቦቃ ወጣት ክርስቲያን ነው ። ትዳር እንደያዘ ብዙ ሳይቆይ ሚስቱ በጠና ታመመች ። አንዳንድ ሰዎች ሰቦቃን ሚስትህ ልትድን የምትችለው መጽሐፍ ገላጭ ቢረዳት ብቻ ነው ብለው ነገሩት ። ሰቦቃም ወደ መጽሐፍ ገላጭ ቤት ሄደ ። መጽሐፍ ገላጩም የሕመሟ ምክንያት የሰቦቃ እናት ውቃቢ እንደሆነና ሊሻላትም የሚችለው ለእናቱ ውቃቢ አንድ በሃ በግ ቢያርድ መሆኑን ገልጦ ነገረው ። ሰቦቃም እንደተነገረው አደረገ ፤ በዚህም ከእውነት እየራቀ ሄደ ።



አሁን መጽሐፍ ቅዱስህን አውጣና ያዕቆብ 5፥19—20 አንብብ ።

---

3. ሰቦቃ ከእውነት ርቆ እግዚአብሔርን መከተል ተወ ። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ አንዳንድ ሰዎች በሰቦቃ ላይ በቁጣ ተነሡ ። ስለ እርሱ ክፉ ማውራት ሰለጀመሩ እርሱን መርዳትም ሆነ መጠየቅ አቋረጡ ።

ያዕቆብ አንድ ክርስቲያን ወንድም ከእውነት እየራቀ ሲሄድ ምን ማድረግ ይገባናል ይላል ? ____________________

____________________________________________

---

4. ያዕቆብ መልሰን ወደ እውነት ልናመጣው ይገባናል ይላል ። ሰቦቃ በእምነቱ ብርቱ ስላልነበረ በቤቱ በሽታ በገባ ጊዜ በፈተና ወደቀ ። ያዕቆብ ሰቦቃን ማማት ወይም ስለ እርሱ ክፉ ማውራት አይገባንም ይላል ። አንድ ሰው ሲደክም በማማት ፈንታ ወደ እርሱ ሄደን እርዳታ ልናደርግለት ይገባናል ። ልናዋየውና አብረነው ልንጸልይ ይገባናል ። ትክክለኛውንም መንገድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማሳየት ይገባናል ።

4. የእምነታችን በመከራ መፈተን የሚረዳን እንዴት ነው ? ______

5. ፈተና ሲገጥመን ምን ሊሰማን ይገባል[?] ______

6. አንዱ የፈተና ምንጭ ዲያብሎስ ነው ። ሌላውስ የፈተና ምንጭ ምንድር ነው ? ______

7. ያዕቆብ በሕይወታችን ውስጥ ኃጢአት እንዲነግሥ ብንፈቅድ ምን ይሆናል አለ ? ______

8. መጽሐፍ ቅዱስህን ሳትመለከት ያዕቆብ 1፥19—20 ጻፍ ። ______

9. ንጹሕ ሃይማኖትን የሚያመለክቱ ሁለት ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

   ሀ) ______

   ለ) ______

---

ከ2ኛው ሳምንት ትምህርት የወጡ ጥያቄዎች

10. በሰዎች መካከል ብናዳላ ምን እንፈጽማለን ? ______

11. ስለ ባልንጀራ የተነገረው የንጉሡ ሕግ ምንድር ነው ? ______

12. መጽሐፍ ቅዱስህን ሳትመለከት ያዕቆብ 2፥17 ጻፍ ። ______



13. አንድ ሰው እምነቱ ሕያውና እውነተኛ መሆኑን ለማሳየት ምን ሊኖረው ይገባል ? ______

14. ያዕቆብ ምላሳችንን በምን ታላቅ ነገር ይመስለዋል ? ______

15. ከያዕቆብ መጽሐፍ እንደምናገኘው ፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠብ የሚያስነሣው የመጀመሪያው ነገር ምንድር ነው ? ______

16. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጠብ የሚያስነሡ ሦስቱ ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

   ሀ) ______

   ለ) ______

   ሐ) ______

17. ያዕቆብ በሚነግረን መሠረት ፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚነሣውን ጠብ ለማቆም ልናደርጋቸው የሚገቡን ሦስት ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

   ሀ) ______

   ለ) ______

   ሐ) ______

---

## ከ3ኛው ሳምንት ትምህርት የወጡ ጥያቄዎች

18. ገንዘብን መውደድ ሰዎች ምን እንዲሆኑ ያደርጋል ?

    ሀ) ____________________

    ለ) ____________________

19. ያዕቆብ ክርስቲያኖች የጌታን መመለስ እንዴት መጠበቅ ይገባቸዋል ይላል ? ____________________

____________________________________________

20. ያዕቆብ በመከራ ውስጥ ስንሆን ከብሉይ ኪዳን የማንን ምሳሌነት እንከተል ይላል ? ____________________

____________________________________________

21. ክርስቲያኖች መማል የማይገባቸው ለምንድር ነው ?

    ሀ) ____________________

    ለ) ____________________

22. በሕመም ጊዜ ልናደርጋቸው የሚገቡን ሦስት ነገሮች ምንና ምን ናቸው ?

    ሀ) ____________________

    ለ) ____________________

    ሐ) ____________________

23. ያዕቆብ አንድ ክርስቲያን ወንድም ከእውነት እየ ራቀ ሲሄድ ምን ማድረግ ይገባናል ይላል ? ______

____________________________________________